የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 1
ADDIS ABABA, 25th October, 2016

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱ ዓ.ም

የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ.........................................................ገፅ ፱ሺ፫፻፷፱

## CONTENT

Proclamation No.1/2016

State of Emergency Proclamation for the Maintenance of Public Peace and Security ..............................page 9369

## አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱

## የሕዝብን ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

መንግስት ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን የመጠበቅ፣ የሀገርን ሠላምና ህልውና፣ የሕዝብንና የዜጎችን ደህንነት የማረጋገጥ እና ኢንቨስትመንትና መሠረተ ልማቶችን ከጥቃት የመጠበቅ ሕገመንግስታዊ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ፤

ሕገ መንግስታዊ ሥርአቱን፣ የሕዝብን ሠላምና ፀጥታ አደጋ ላይ የሚጥሉ በተለይም የኢንቨስትመንትና የልማት እንቅስቃሴን በማዳከም ላይ ያነጣጠሩ በአንዳንድ የሀገራችን አካባቢዎች በውጭ ሀይሎች ድጋፍ ጭምር የተፈፀሙ ሕገወጥ ተግባራት ለበርካታ ሰዎች ህይወት መጥፋት፣ ለተቋማት እና መሠረተ ልማቶች መውደም እንዲሁም ለብጥብጥና ሥርዓት አልበኝነት ምክንያት መሆናቸውን እና ይህን ሁኔታ በመደበኛው የሕግ ማስከበር ሥርዓት ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከማይቻልበት ደረጃ ላይ መደረሱን በመረዳት፤

## PROCLAMATION No.1/2016

## STATE OF EMERGENCY PROCLAMATION FOR THE MAINTENANCE OF PUBLIC PEACE AND SECURITY

**RECOGNISING** the constitutional responsibility of the State to maintain the constitutional order, ensure peace and security of the country, protect security of the public and citizens, protect investment and infrastructure from attack;

**RECOGNISING** that illegal activities committed in some parts of the country even with the support of foreign forces have caused the loss of lives of many people, destruction of institutions and infrastructures, unrest and disorder and endangering the constitutional order, public peace and security specially targeting to weaken investment and development activities and that this situation has reached a level where it cannot be prevented and controlled through the regular law enforcement mechanism;

እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ ለመቆጣጠር እና ሕገመንግስታዊ ሥርዓቱን ለመጠበቅ ልዩ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማውጣት እንደሚያስፈልግ በሕገመንግስቱ የተደነገገ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀፅ ፺፫(፩)(ሀ) መሠረት የሚከተለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጇል::

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### ፪. ትርጓሜ

ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል:-

፩/ "የሕግ አስከባሪ አካል" ማለት የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የክልል ፖሊስ እና ሌሎች የፀጥታ አካላት ነው፤

፪/ "የመርማሪ ቦርድ" ማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ ፺፫ (፭) የተመለከተው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ ነው፤

፫/ "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት" ማለት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ መሠረት የተቋቋመ የአስቸኳይ ጊዜ አስፈፃሚ ኮማንድ ፖስት ነው፤

፬/ "ሕግ" ማለት የፌደራል ሕገ መንግስት፣ እንደአግባብነቱ በፌደራል ወይም በክልል መንግስታት ሕግ አውጪ ወይም ሥልጣን ባለው ሕግ አስፈፃሚ አካል የወጣ የክልል ሕገመንግስት፣ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ነው፤

**WHEREAS,** it has been proclaimed in the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia that it is necessary to decree a state of emergency proclamation that enables the taking of special measures to control such kind of situation and to protect the constitutional order;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 93(1)(a) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "State of Emergency Proclamation for the Maintenance of Public Peace and Security No.1/2016".

### 2. Definition

For the purposes of this Proclamation:

1/ "law enforcement organ" means Ministry of Defence, National Intelligence and Security Service, Federal Police Commission, Regional Sates Police and other security organs;

2/ "Inquiry Board" means the State of Emergency Inquiry Board indicated under Article 93(5) of the Constitution;

3/ "State of Emergency Command Post" means state of emergency executing command post established under Article 6 of this Proclamation;

4/ "law" means the Federal Constitution or Regional Constitution, Proclamation, regulation and directive enacted by the respective Federal or Regional state law making body or authorized executive organ;

፭/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፮/ በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለፀው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል::

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

፩/ ይህ አዋጅ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪/ በአዋጁ መሠረት የሚወሰድ እርምጃ ተግባራዊ ወይም ቀሪ የሚሆንበትን አካባቢ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስቱ ይወስናል፣ ይህንኑ ለሕዝብ ያሳውቃል::

## ክፍል ሁለት

## በአስቸኳይ ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎችና የማይፈቀዱ ተግባራት

**፬. <u>በአስቸኳይ ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎች</u>**

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስቱ ሕገ መንግስታዊ ሥርአቱን ለማስከበርና የሕዝብና የዜጎች ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን:-

፩/ ማንኛውም ሁከት፣ ብጥብጥና በሕዝቦች መካከል መጠራጠርና መቃቃር የሚፈጥር ይፋዊ ሆነ የድብቅ ቅስቀሳ ማድረግ፣ ፅሁፍ ማዘጋጀት፣ ማተምና ማሰራጨት፣ ትእይንት ማሳየት፣ በምልክት መግለፅ ወይም መልዕክትን በማናቸውም ሌላ መንገድ ለህዝብ ይፋ ማድረግ ሊከለክል ይችላል፣

፪/ ማናቸውም የመገናኛ ዘዴ እንዲዘጋ ወይም እንዲቋረጥ ሊያደርግ ይችላል፣

፫/ የሕዝብና የዜጎች ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ ሲባል ስብሰባና ሰልፍ ማድረግ፣ መደራጀት፣ በቡድን ሆኖ መንቀሳቀስ ሊከለክል ይችላል፣

5/ "person" means any physical or juridical person;

6/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Scope of Application</u>**

1/ This Proclamation shall be applicable in all parts of the country.

2/ The State of Emergency Command Post shall determine areas within which measure in accordance with this Proclamation shall be taken or withdrawn, and publicise the same to the public.

## PART TWO

## EMERGENCY MEASURES AND PROHIBITED ACTIONS

**4. <u>State of Emergency Measures</u>**

When the Emergency Command Post believes that it is necessary for the observance of the constitutional order and for maintenance of peace and security of the public and citizens, it may:

1/ prohibit hidden or public incitement, preparing, producing, publishing or distributing writings or displaying a show, demonstrating through sign or making message public through any medium that causes riot, disturbance and suspicion or grievance among people;

2/ cause the closure or termination of any means of communication;

3/ prohibit assembly, demonstration or moving in a group or associating with the view to maintain peace and security of the people and citizens;

፬/ የሕዝብን ሠላምና ፀጥታ በማደፍረስ ተግባር ላይ ተሳትፏል ብሎ የሚጠረጥረውን ማናቸውም ሰው ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በቁጥጥር ሥር ለማድረግ፣ እያጣራ ወይም እያስተማረ ለመልቀቅ፣ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ሆኖ ባለበት ጊዜ ድረስ ይዞ ለማቆየት ወይም በመደበኛ ሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግ ይችላል፣

፭/ ወንጀል የተፈፀመባቸውን ወይም ሊፈፀምባቸው የሚችሉ ዕቃዎችን ለመያዝ ሲባል ማናቸውንም ቤት፣ ቦታ፣ መጓጓዣ ለመበርበርና እንዲሁም ማናቸውንም ሰው ለማስቆም፣ ማንነቱን ለመጠየቅ፣ ለመፈተሽ ይችላል፤ በብርበራ ወይም በፍተሻ የተያዙ ዕቃዎችን በማስረጃነት ለፍርድ ቤት መቅረባቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጣርተው ለባለመብቱ ይመለሳል፣

፮/ የሰዓት እላፊ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ይወስናል፤ ለተወሰነ ጊዜ አንድን መንገድ፣ አገልግሎት መስጫ ተቋም ለመዝጋት እንዲሁም ሰዎች ለጊዜው በተወሰነ ቦታ እንዲቆዩ፣ ወደ ተወሰነ አካባቢ እንዳይገቡ ወይም ከተወሰነ ቦታ እንዲለቁ ለማዘዝ ይችላል፣

፯/ የተቋማትና የመሠረተ ልማቶች ጥበቃ ሁኔታን ይወስናል፣

፰/ የሕዝብና የዜጎች ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ ሲባል የጦር መሣሪያ፣ ስለት ወይም እሳት የሚያስነሱ ነገሮችን ይዞ መንቀሳቀስ የማይቻልባቸውን ቦታዎች ለይቶ ሊወስን ይችላል፣

፱/ በሠላም መደፍረስ ምክንያት የፈረሱ የተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች ከሚመለከተው ክልል እና ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር በመተባበር መልሶ እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣

4/ arrest any person without a court warrant upon suspicion that he has taken part in activities that cause disturbance to the peace and security of the people; release through screening or by educating; or detain while this Proclamation is in force or hold the same accountable under the regular law;

5/ search with a view to seize any material used or may be used to perpetrate a crime, any house, place and carrier; stop any person to search and to ascertain his identity; return the objects seized to the person entitled or present to a court as evidence after screening;

6/ determine condition under which curfew may be imposed; give order for the closure of a given street or a service providing institution for limited period of time; or give order for persons to stay in a certain place, ban from entering into or evacuate from a given place;

7/ determine security protection conditions of institutions and infrastructures;

8/ identify and determine for the purpose of maintaining public and citizen's peace and security, areas in which mobility with weapon, knife and inflammable materials is prohibited;

9/ reorganize administrative bodies of different hierarchies dismantled due to turbulences in cooperation with the concerned Region and local community;

፲/ ሕዝብ የሚጠቀምባቸውን ወይም ፈቃድ የወጣባቸው የንግድ ሥራዎች ወይም የመንግስት ተቋማት እንዳይዘጉ፣ አገልግሎት እንዲሰጡ ወይም የሥራ ማቆም እንዳይደረግ ሊያዝ ይችላል፣

፲፩/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎችን ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ሀይል ለመጠቀም ይችላል፣

፲፪/ ኃላፊነቱን ለመፈፀም ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ይፈፅማል::

## ፭. የማይፈቀዱ ተግባራት

ማናቸውም የሕግ አስከባሪ አካል እና ባልደረባ በዚህ አዋጅ አፈፃፀም ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ ፩ የተመለከተውን የመንግስት ስያሜ መቀየር፣ በአንቀፅ ፲፰ የተመለከተውን ኢሰብአዊ አያያዝ መፈፀም፣ በአንቀጽ ፳፭ የተመለከተውን የሰዎችን የእኩልነት መብት የሚጥስ ተግባር መፈፀም፣ በአንቀፅ ፴፱(፩) እና (፪) የተመለከተውን የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን መብት መጣስ የተከለከለ ነው::

## ክፍል ሶስት
## የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት እና የመርማሪ ቦርድ መቋቋምና ሀላፊነት

## ፮. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት መቋቋምና ኃላፊነት

፩/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን የሚያስፈፅም በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ አግባብነት ካላቸው አካላት የተውጣጣ አባላትን የያዘ (ከዚህ በኋላ “የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት” ተብሎ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስቱን አባላት ይመርጣል፡፡

፫/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተመለከቱ ተግባራትን

10/ give order not to close licensed businesses or government organizations that the public utilizes, to provide service or not to halt work;

11/ may use proportional force which it finds necessary for the execution of state of emergency measures provided in this Proclamation;

12/ carry out other necessary activities to discharge its responsibilities.

## 5. Prohibited Activities

Any law enforcement organ or its officials shall, in the application of this Proclamation, be prohibited to change the name of the government, to commit inhuman and degrading treatment, to perform any activity violating the right to equality and to transgress the right of nation, nationalities and people in contravention to the provisions of Article 1, 18, 25 and 39 (1) and (2) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia

## PART THREE
## STATE OF EMERGENCY COMMAND POST AND INQUIRY BOARD ESTABLISHMENT AND RESPONSIBILITY

## 6. State of Emergency Command Post Establishment and Responsibility

1/ A body composed of members from relevant bodies and led by the Prime Minister hereinafter referred to as “State of Emergency Command Post’’ is hereby established that enforces the State of Emergency Proclamation.

2/ The Prime Minister shall select members of the State of Emergency Command Post.

3/ State of Emergency Command Post leads and enforces activities mentioned under Article 4 of

በበላይነት ይመራል፣ ያስፈፅማል፡፡

፬/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስቱ የሕግ አስከባሪ አካላትን በአንድ እዝ ስር አድርጎ በላይነት ይመራል፣ ያዛል::

## ፯. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስቱ ግዴታ

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስቱ በቁጥጥር ሥር የተደረጉ ሰዎችን ስም እና የሚቆዩበትን ቦታ ለመርማሪ ቦርዱ ያሳውቃል::

## ፰. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ

፩/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የመርማሪ ቦርዱ ሰባት አባላት የሚኖሩት ሲሆን፣ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትና ከሕግ ባለሙያዎች የተውጣጡ ሆነው በምክር ቤቱ ይመደባሉ::

## ፱. የመርማሪ ቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

መርማሪ ቦርዱ:-

፩/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት የታሰሩትን ግለሰቦች ስም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ያደርጋል፣ የታሰሩበትን ምክንያት ይገልፃል፣

፪/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት የሚወሰዱት እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ ኢሰብአዊ እንዳይሆኑ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣

፫/ ማናቸውም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃ ኢሰብአዊ መሆኑን ሲያምንበት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት እርምጃውን እንዲያስተካክል ሀሳብ ይሰጣል፣

፬/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃዎች ኢሰብአዊ ድርጊት የሚፈፅሙትን ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ያደርጋል፣

፭/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲቀጥል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለውን አስተያየት ለምክር ቤቱ ያቀርባል::

this Proclamation.



4/ State of Emergency Command Post leads under one command and orders law enforcement organs.

## 7. Duties of the State of Emergency Command Post

The State of Emergency Command Post shall notify the Inquiry Board the names of arrested persons and the place where they are detained.

## 8. State of Emergency Inquiry Board

1/ State of Emergency Inquiry Board is hereby established.

2/ The Inquiry Board shall comprise seven members to be chosen and assigned by the House of Peoples' Representatives from among its members and from legal experts.

## 9. Power and Responsibilities of the Inquiry Board

The Inquiry Board shall:

1/ make public within one month the names of all individuals arrested on account of the state of emergency together with the reason for their arrest;

2/ inspect and follow up the measures taken during the state of emergency are by no means inhuman;

3/ recommend to the Prime Minister or to the Council of Ministers to take corrective measures if it finds any case of inhuman treatment during state of emergence measures;

4/ ensure the prosecution of perpetrators for committing inhuman act during the state of emergency measures;

5/ submit its views to the House of Peoples' Representatives on a request to extend the duration of the state of emergency.

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲. ተፈፃሚነታቸው የታገዱ ሕጎች**

በቪዬና ኮንቬንሽን የተመለከተው የዲፕሎማቲክ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ የፍሬ ነገርና የሥነ-ሥርዓት ሕጎች ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ይህ አዋጅ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜያት ተፈፃሚነታቸው ታግዶ ይቆያል::

**፲፩.የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ አፈፃፀም እንዲሁም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስቱ እና የሕግ አስከባሪ አካልና ባልደረባ የሚወስዷቸውን የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች የማክበርና ለዚሁ የመተባበር ግዴታ አለበት::

**፲፪.የወንጀል ተጠያቂነት**

፩/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ከአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች ጋር የተያያዙ ግዴታዎችን ተላልፎ የተገኘ ማናቸውም ሰው እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ የተመለከተውን የመተባበር ግዴታ የጣሰ ማንኛውም ሰው እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል::

**፲፫.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ያወጣል፡፡

፪/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት አዋጁንና በአዋጁ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ያወጣል::

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**10. Suspended Laws**

Without prejudice to diplomatic immunities provided for under the Vienna Convention, substantive and procedural laws inconsistent with this Proclamation shall remain suspended during the implementation of this Proclamation.

**11. Duty to Cooperate**

Any person has the duty to respect the implementation of this Proclamation and state of emergency measures taken by the emergency command post and law enforcement organ or its officials and cooperate there with.

**12. Criminal Liability**

1/ Whosoever violates obligations related with the state of emergency measures shall be punishable with rigorous imprisonment of up to five years.

2/ Whosoever violates the duty to cooperate as provided under Article 11 of this Proclamation shall be punishable with simple imprisonment up to three years.

**13. Power to Issue Regulations and Directives**

1/ The Council of Ministers shall issue regulation for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The State of Emergency Command Post shall issue directive for the implementation of this Proclamation and regulation issued pursuant to this Proclamation.

**፲፬.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

፩/ ይህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ ለስድስት ወራት የፀና ይሆናል፡፡

፪/ የስድስት ወር ጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ በፊት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስቱ የአዋጁ ተፈፀሚነት ቀሪ የሚሆንበትን ጊዜ ሊወስን ይችላል፡፡

፫/ ይህ አዋጅ በሕገመንግስቱ አንቀጽ ፺፫(፪)(ለ) መሠረት በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተቀባይነት እንዲያገኝ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፬/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የስድስት ወር ጊዜ ገደቡ ሲጠናቀቅ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጊዜ ገደቡ በየአራት ወሩ እንዲታደስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፭/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጁን በመገናኛ ብዙሀን ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል::

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**14. Effective Date**

1/ This State of Emergency Proclamation shall remain in effect for six months starting from its promulgation by the Council of Ministers.

2/ The State of Emergency Command Post may determine the cessation time of this Proclamation before the end of the six months period.

3/ This Proclamation shall be presented to the House of Peoples Representatives within fifteen days for its approval in accordance with Article 93(2)(b) of the Constitution.

4/ The House of Peoples Representatives may renew the time limit every four months when the time limit ends and when it finds it necessary.

5/ The Prime Minister shall declare the promulgation of this State of Emergency Proclamation through the mass media.

**Done at Addis Ababa, this 25th day of October 2016.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**